# የጠ/ሚኒስትሩን መንግሥት ራሱ የሾማቸው ሰዎች እየገዘገዙት ነው!

*ነፃነት ዘለቀ*

*አሁንስ የዚህችን ሀገር ነገር ወደማልሰማበትና ወደማላይበት ቦታ የሚወስደኝ ባገኘሁ፡፡ ሰው ወደ ፊት መሄድ ቢያቅተው እንዴት ባለበት መርገጥ እንኳን ይቸግረዋል? ከወያኔ መማር ባይቻል ካሳለፉት የመከራና የስቃይ ሕይወት መማር እንዴት ያቅታል? የወያኔን ስህተት በመድገም ለወያኔ ሁለንተናዊ የጥፋት ዘመቻ ዱላ ማቀበል በውነቱ ጊዜው የሚፈቅደው ብልኅነት ነው ወይ? ሞኝነትና ራስ ወዳድነት ልክ ሊኖራቸው አይገባምን?*

*የወያኔን ስህተት መድገም የመጨረሻ ድንቅርና ነው፡፡ ወያኔ ለምን እንደወደቀ ማሰብ አለመፈለግ ትልቁ አላዋቂነት ወይም ድድብና ነው፡፡ ይህን ያሳለፍነውን የወያኔ አገዛዝ በአንድ ወይ በሌላ መልክ ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር በእሳት እንደመጫወት ነው፡፡ ከይሉኝታ አጥር ወጥታችሁ ይህን መጥፎ አካሄድ ሁላችሁም ልብ አድርጉ!*

*የማንኛውም ክፉ ነገር የውድቀት መንስኤ በራሱ ውስጥ ይገኛል፡፡ ለምሣሌ ሕወሓት መውደቅ የጀመረው ገና ሲፈጠር ነው፡፡ ያ አብሮት የተፈጠረ የውድቀት መንስኤው በውስጡ ተደብቆ አንዴ ከፍ ሌላ ጊዜ ዝቅ ሲል ኖረና በመጨረሻ ግዘፍ ነስቶ በቅርቡ አንደባሎ ጣለው - ከአሁን በኋላ ወያኔ ያንሠራራል ማለት ታሪክም እግዚአብሔርም የሉም ብሎ እንደመወራረድ ነው - አይሆንም፡፡  እንደቲቤታውያን የቡድሂዝም እምነት በሌላ መልክ ካልተፈጠረ በስተቀር የአንድ ፍጡር ዕድሜ አንድ ነው፡፡ ደርግም፣ ወያኔም፣ አንተም እኔም ሳንቀር በውስጣችን መጨረሻችንን ጠቋሚ የሞት መርዶ ይዘን ተወልደናል፡፡ ይህን ክስተት የግሪክ ፈላስፎች nemesis ይሉታል፡፡ ስትወለድ ከሞት ጋር ነው፤ ስትከብር ከድህነት ጋር ነው፤ ስትገን ከውርደት ጋር ነው፤ ስትፋፋ ከክሳት ጋር ነው - ከፍታን ካለዝቅታ አታስበውም፤ ቀጭን ያለው ወፍራም ስላለ ነው፤ ብርሃን ባይኖር ጨለማን አታውቅም፡፡ በአጥፊና ጠፊ ትስስር አንዱ ድብቅ ሲሆን ሌላው ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ የሁለትዮሻዊውን ንጽጽራዊ ጉዞ ካላወቅህ ተሞኝተሃል፡፡ እናም ክፉ ወይም መጥፎ ሰው ከሆንክ በጊዜ ሂደት ገዝግዞ የሚጥልህ የምትከተለው ክፉ ነገር ተፃራሪና የ"Binary Opposition"አንዱ ውጤት የሆነው መልካም ነገር የሚያሳድርብህ የበቀል ጽላሎት ነው፡፡ ስለዚህ ወንድሜ ቢቻልህስ መልካም ነገር ሠርተህ ተኩራራ እንጂ በመጥፎ ነገር አትጀነን - ውሎ ሳያድር ብድሩን ከጎንህ ታገኘዋለህና፡፡ "የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ"ን አስባት፡፡ አዲስ ነገር እየነገርኩህ ሳይሆን የምታውቀውን እያስታወስኩህ ነው፡፡*

*የዶ/ር ዐቢይን መንግሥት ከሚደግፉት መካከል ነኝ - ሊያውም በዋናነት፡፡ አልቃወምም ማለት ግን አይደለም፡፡ ይሄ "እገሌ ከእገሌ ይሻላል፤ ከእገሌ ስለማይብስ እገሌን ሳናንገራግር እንደግፈው፣ ‹ሆ! ያ እ የለዪለት ሰይጣን ነበር› …" እየተባለ በጭፍን የሚደረገውን ድጋፍም ሆነ ነቀፋ አልስማማበትም፡፡ በዚህ ረገድ የማልስማማባቸው ጉዳዮች ሲገጥሙኝ ወይ ስታዘነብ እንደምንጊዜውም እጮሃለሁ፡፡ በዚህም ቢያንስ የኅሊና እርካታ አገኛለሁ፡፡ ለፍርዱ ደግሞ ፈጣሪን እጠብቃለለሁ - ለምንነው አፍረን አናውቅምና ለጊዜው እኛ አንጠቀም እንጂ ፈጣሪ የመጨረሻ ፍርዱን መስጠቱ ደግሞ አይቀርም፡፡ ያny ሁሉም ቢያዝን ታዲያ ምን ፋይዳ አለው?*

*ትናንት ኢትዮጲስ ጋዜጣን ሳነብ የተመለከትኩት ዜና በእጅጉ አሳዝኖኛል፡፡ "የለማኝ ስልቻ ቢንከባለል እለማኝ ደጅ አረፈ" እንደሚባለው የዕድላችን እየከፋና ይበልጥ እየተጣመመ መምጣትም አሳስቦኛል፡፡ ከማዘጋጃ ቤት በዘራቸው ምክንያት ከሥራ ስለተባረሩት ወይም "አዲስ የሥራ ድልድል እስኪነገራችሁ በየቤታችሁ ቆዩ" ስለተባሉት ምስኪን ዜጎች  የተዘገበውን አስራሚ ዜና አንብቡት፡፡ ይህን መሰል የዘረኛ አካሄድ ከአሁን በፊት በቅርቡ በስፖርት ኮሚሽን እንደተፈጸመ አንብበናል፡፡ ይህ አካሄድ "ብጥለው ገለበጠኝ" ዓይነት የወያኔን ስህተት በኮፒ-ፔስት እንዳለ የመድገም አሣፋሪ ድርጊት ነው፡፡ ዛሬ የምንሠራት እያንዳንዷ ስህተት ተጠራቅማ ወንዝ ትሆንና ወንዙም ጎርፍ ይፈጥርና ወደማንወጣው አዘቅት እንደሚከተን ካላወቅን ለጊዜው የምንፈልገውን ነገር ማድረግ ስለቻልን ብቻ ብናደርግ የኋላ ኋላ ተያይዘን መጥፋት የማይቀርልን የመጨረሻ ዕጣ ፋንታ ይሆናል፡፡ ሞኝነት ደግሞ ከዚህ በላይ የለም - ገደብ የሌለው ሞኝነት ደግሞ መጨረሻው አያምርም፡፡ እጃችን ውስጥ የገባን ወርቃማ ዕድል በዚህ መልክ*

አልኮስኩሰን ካበላሸነው ዕንቁላልን ከ21 ቀናት በላይ ታቅፋ ጫጩቶቿን ለማግማት እንዳቀደች ጅላጅል ዶሮ መሆን ነው- ለሁሉም ጊዜ አለው፡፡ የጊዜን ቀመር አለማወቅ ለውድቀት ይዳርጋል፡፡ በጨው ደንደስ ሊወደስ የሚፈልግ በርበሬ ደግሞ የጨውን ውለታ ረስቶ ያን ያህል ሊቀናጣና ትዝብት ውስጥ ሊወድቅ አይገባም፡፡ ስንተዋወቅ ባንተናነቅ ጥሩ ነው - ለማንኛውም፡፡

ዶ/ር ዐቢይ ኢንጂነር ታከለ ኡማን ሲሾም የሹመት አሰጣጡ ሂደት አግባብ እንዳልነበረ ብዙዎች ጨኸዋል፡፡ የጩኸታቸው ምንጭ ደግሞ ዘረኝነት ሳይሆን በወጣቱ ሹም የአመለካከት መስመር ዙሪያ ይወራ የነበረው የtrack record (ግለ ታሪክ) ውዝግብና እና ከዚያን ጊዜ በፊት ወጣቱ ተሾሞባቸው በነበሩ የአዲስ አበባ ዙሪያ አነስተኛ ከተሞች አከናወናቸው የተባሉ አንዳንድ ለጊዜው ተጨባጭ ማስረጃ ላስቀምጥባቸው የማይቻሉኝ የሙስና ተግባራት ናቸው፡፡ ሚዲያዎች ሲጮኹ የሚሰማ የመንግሥት አካላት ቢኖግሮች በወቅቱ ይቀጩ ነበር፡፡ ዝም መባላቸው ግን የተለዩ ምሥጢር ምናልባትም ከላይ እስከታች የተዘረጋ አንዳች ትስስር መኖሩን ጠቋሚ ነው፡፡

ለማንኛውም የተሰጡት አስተያየቶች ከቁብ ሳይጣፉ ቀርተው ሹመቱ ቀጠለ - መንግሥታዊው ሕዝብን የመናቅ አባዜም እንደነበረው መቀጠሉን በእግረ መንገድ ልብ ይሏል ታዲያ፡፡ አሁን ደግሞ ሰው በዘሩ እየተመረጠ በለፋባት የእኩል ሀገሩ አንዱ መጤና ተባራሪ ሌላው ባለሀገርና ተጠቃሚ እየሆነ ነው፡፡ ይህ እስከመቼ ይቀጥላል? ዶ/ር ዐቢይስ እንዲህ ዓይነት ቅሬታዎችን እያወቀ እንዳላወቀ በመሆን እስከመቼ ሕዝብ በቅሬታ እንደተዋጠ በ"እህህ" እና በ"ወይኔ!" ይኖራል? የሀገራችን ጉዳይ ሁላችንንም ያገባናልና እንጠይቅ፡፡ የምን መተፋፈር ነው?! ድጋፋችንንና ፍቅራችንን እንደሞኝነት በመቁጠር እኛን በይሉኝታ ገመድ አስረው ወደ ገደል ሊከቱን የቋመጡ ኃይሎች አሉ፡፡

አዎ፣ መንግሥት የሚወድቀው በአንድ አዳር አይደለም ወይም እንዲሆንም አይጠበቅም፡፡ የመገዝገዣ ጊዜ እንዳለ የመውደቂያም ጊዜ አለ፡፡ ትዕቢትና ትምክህትም ተፀንሰው እንደሚወለዱ ሁሉ ታመው የሚሞቱበት የማይቀር ተፈጥሯዊ ክስተትም አለ፡፡ "ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ" ወይም "መቼ መጣሽ ሙሽራ፣ መቼ ቆረጠምሽ ሽምብራ" እንዲሉ ይህ በሕዝብ ዘንድ በእፍፍፍ ፍቅር እየታየ ያለ የለውጥ ኃይል የወያኔን ስህተት እየደገመ መቀጠሉ የማይቀር ከሆነ አወዳደቁ እንደሮም እንደሚሆን አይጠረጠርምና ለኛም ለርሱም ሲል ጥንቃቄ ያድርግ፡፡ ስህተትን መደጋገም ስህተትን አያርምምና በብርቱ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ የዕንባን ዱላና የጸሎትን ኃይል ለማወቅ ብዙ ርቀት መጓዝ አያስፈልግም - ደርግንና ወያኔን ማስታወስ ብቻ ይበቃል፡፡ እንደማሽላ እንጀራ ሲሽመደመዱ አይተናል - በንፋስ ብቻ! መጽሐፉ "ትዕቢት ሞትን ትቀድማለች" ይላልና ቆሞ ያለ የሚመስለው ይጠንቀቅ ይልቁንስ፡፡ ሴትዮዋ ልጁ ለጠየቀቻት የእጅ ማሳከክ ምልክት "እኔም በአንድ ቀን አልተቀመጥኩም" ያለችው ወድዳ አልነበረም - የተረቱን እማሬያዊ ተራ አሉባልታ ተውትና ፍካሬያዊ ፍቺውን ብቻ ተረዱልኝ፡፡ ነገር አልወድም፤ ሰልችቶኛል፡፡

አምባገነንት ይወለዳል፤ ምቹ ሁኔታ ካገኘ አድጎ ለቁም ነገር ይደርሳል፡፡ አንድ ሕዝብ አምባገነንነትን ይፀንሰዋል፤ ይወልደዋልም፡፡ ለዐይን ይበጃል ያሉት ኩል ዐይንን ሊያጠፋ እንደሚችል ሁሉ እልል ብለህ ያዋለድከው መልካም የሚመስል የዴሞክራሲ ጽንስም በአንዳች ተዓምር ተለውጦ አምባገነን ሥርዓትን ሊፈጥር ይችላልና በዋል ፈሰስ መሆን ደግ እንዳልሆነ እንገንዘብ - "ጠርጥር ገንፎም አለው ስንጥር" ይባላል፡፡ በሩቁም በቅርቡም ታሪካችን ቁጭ ብለን የሰቀልናቸው ብዙ ነገሮች ቆመን ማውረድ ያቀታን በዚህ መልክ ነው፡፡

እኛ ደግሞ ብዙ ስለተሰቃየን ከአሁን በኋላ ለአምባገነንትም ሆነ ለክፋትና ለመጥፎ ሕይወት የምናባክነው ጊዜ ሊኖረን አይገባም፡፡ ተፈቃቅረንና ተስማምተን መኖር እየቻልን ስህተትን በስህተት በመተካት ልንሰቃይ አይገባንም፡፡ በጥሩ ሁኔታ መኖር ስንችልም በክፉዎች ምርጫ ውስጥ ገብተን "ከዚህኛው ክፉ ያኛው ክፉ ይሻለናል" በሚል የመጥፎዎችና ክፉዎች ምርጫ ውስጥ ተዘፍቀን መዳከር የለብንም፡፡ እኛም እኮ ሰዎች ነን!

ይህን መልእክቴን የማታስተናግዱ የሁለት ዓለም ሚዲያዎች እንዳላችሁ አውቃለሁ፡፡ ይህም ስህተት ነው፡፡ እንደቁራ የምንጮኸው ወደን አይደለም፡፡ ወደ እሳት ባህር እያስመጠን የሚገኝን አሳዛኝ ሁኔታ አለማስተናገድ "ተወው፤ የኔን እግር እየበላ ነው" እንደተባለው የጅቡና የፈሪዎች ታሪክ የሚመስል ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ አሳዛኝ

በሆነ የነገሮች ሂደት ውስጥ ትገኛለችና ይህን መልእክቴን ለሁሉም በማዳረስ ረገድ ሁሉም ይተባበር፡፡ እንዲህ የምለው ለእገሌ ዘር ወይም ለእገሌ ቡድን በማዳላት ወይ ለማዳላት በመፈለግ አይደለም፡፡ ለአክስቴና ለአጎቴም አይደለም፡፡ ይህ የመሰለው ክስተት ለማንኛውም የፖለቲካ ቡድን - በዋናነት ለአድራጊውም ጭምር - ጠቃሚ አይደለምና ሁላችንም እንጨህበት፡፡ አንዳንዴ ጩኸትም ዋጋ አለውና - ኢያሪኮን ማሰብ ይቻላል፡፡

netsanetz28@gmail.com